# የለውጥ ተምሳሌት ለመሆን የበቃ የልማት አቅጣጫ

ተረፈ ኃይሌ 09-13-14

ኢትዮጵያ ለግብርና ልማት የታደለች አገር መሆኗ ሲነገር የኖረ ታሪክ ነው። እጅግ የሚበዛው ህዝቧም ህይወቱን የመሰረተው በዚሁ የተፈጥሮ ፀጋ ላይ እንደሆነም መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚህም በላይ ደግሞ ዘርፉ አጠቃላይ የአገሪቱ ምጣኔ ኃብት ዋልታና ማገር ተደርጎም ይወሰዳል። እንዲያም ሆኖ ግን ይህ የአገርና ህዝብ አለኝታ የሆነው ተፈጥሯዊ ፀጋ ብዙም ጥቅም ላይ ሳይውልና ህዝቡም የትሩፋቱ ተቋዳሽ ሳይሆን እንዲያው እየባከነ ብዙ ዘመናትን ተሻግሯል። አገሪቱና ህዝቦቿም የታላቅ እድገት ምንጭ ሊሆን የሚችለውን ይህንን ኃብት በጉያቸው አቅፈው በድህነትና በችጋር ሲኖሩ አያሌ መቶ ዓመታትን ዘልቀዋል።

በብዙዎች እምነት የግብርና ልማቱ ኋላ ቀር ሆኖ እንዲቀጥልና ተዝቆ የማያልቀው የተፈጥሮ ፀጋ ጥቅም ላይ እንዳይውል ብሎም የአገሪቱ ህዝብ አሳፋሪ ከሆነው የድህነት አዙሪት እንዳይወጣ ካደረጉት ምክንያቶች መካከል አንዱና ምናልባትም ዋነኛው ጠንካራና የህዝብ አለኝታ የሆነ የፖለቲካ አመራርና ይህም የሚመራበት በዜጎች የታመነበት የፖለቲካ ኢኮኖሚ ስርዓት እጦት ነው። የህዝብ ይሁንታን ታድሎ ለአገርና ለወገን የሚያስብ ግልጽ የሆነና ሊተገበር የሚችል ራእይ ባለቤት የሆኑ መሪዎችን አገሪቱ ቀደም ብሎ ታድላ ቢሆን ኖሮ የድህነት ተምሳሌት ተደርጋ ባልተነሳች ነበር ሲሉ የዛሬዎቹ ኢትዮጵያዊያንና  የኢትዮጵያ ወዳጆች ሲገልፁ ይሰማል።

ኢትዮጵያን እስከ 1983 ዓም ማብቂያ ድረስ እየተፈራረቁ ያስተዳደሩት የፖለቲካ ቡድኖች ለተለያዩት የዜጎች ጥያቄዎችና ፍላጎቶች ተገቢውን መልስ ከመስጠት ፈንታ ስልጣናቸውን ለማቀየት ብቻ በመጨነቅ ጥያቄዎቹን በኃይልና በተንኮል ለማኮላሸት የመረጧቸው መንገዶች የእርስ በእርስ ግጭትን የሚያጭሩ፣ በዜጎች መካከል ሊኖር የሚገባውን መተሳሰብና መቻቻልን የሚንዱ ሆነው ቆይተዋል።

ይህም አገሪቱ በድህነት አዘቅት ውስጥ እንድትዋትት፣ ሰላም እንዲርቃትና ዜጎቿም የሚበሉትን አጥተው በርሃብ እንዲሰቃዩ እጣ ፈንታቸው እንዲሆን አድርጎታል፡፡ የቀደሞት መሪዎች ትጋት ስልጣንን እንደጨበጡ መኖርን ብቻ ያለመ በመሆኑም ድህነትን በማሸነፍ ሰላምን ለማምጣት፣ በህዝቦች መካከልም መተማመንንና መቻቻልን ለማጠናከር ይችል የነበረውን የአገር ኃብት መና አስቀርተውት ኖረዋል፡፡ በዚህም የተነሳ ወደፊት መገስገስ ትችል የነበረችውን አገር በማያቋርጥ የኋሊዮሽ ጉዞ ውስጥ ዶለዋታል፡፡

በቅርብ ጊዜ የአገሪቱ ታሪክ ውስጥ ግን ያለማቋረጥ እየተንከባለለ የመጣውን ይህ መጥፎ ገፅታ የሚገታ ጠንካራ መሰረት መገንባት ተጀምሯል፡፡ ወታደራዊው መንግስት በ1983 ዓም ወድቆ አዲስ መንግስት የመሰረቱት ውድ የአገሪቱ ወጣቶች መላው ዜጋ ቆም ብሎና ተረጋግቶ እንዳያስብ ያደረገውን የሰላም እጦት ከማስወገድ ጎን ከፍተኛ ትኩረት ከቸሯቸው ቁልፍ ብሄራዊ ጉዳዮች መካከል ግንባር ቀደሙ የግብርና ልማቱን ማቀላጠፍና ኃብቱን አገር ሊለውጥ የሚችል እሴት እንዲኖረው ማድረግ ነበር፡፡ ይህንን እውን ለማድረግ ደግሞ ሲበዛ ኋላ ቀርና ዚበዛ በተለምዷዊ መንገድ ብቻ የሚሰራበትን የግብርና ስርዓት በተቻለ መጠን ዘመናዊና በጥናትና ምርምር ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይጠይቃል፡፡

አዲሱ የኢትዮጵያ መንግስት መሪዎችም ጊዜ ሳያጠፉም  የወሰዱት እርምጃ በአገሪቱ ተጨባጭ እውነቶች ላይ የተመሰረተ የግብርና ልማትና እድገት ስልትን ቀርጸው ወደተግባር መግባትን ነበር፡፡

በዚህ ስልት አማካኝነትም መላው አርሶ አደሩን ያሳተፈ የግብርና ኤክስቴንሽን መርሃ ግብር ስራ ላይ ዋለ፡፡ በርካታ ንኡስ መርሃ ግብሮችን ያካተተው ይህ መርሃ ግብር የግብርና ስራውን ዘመናዊ ለማድረግ፣ አርሶ አደሩንም በማንቃት ምርታማነቱ እንዲጎለብት የሚያግዙ የተለያዩ ድጋፎችን ይጨምራል፡፡ የተመረጡ ጥቂት አርሶ አደሮችን በመጠቀምም መርሃ ግብሩ ትግበራ ተሞከረ፡፡ የእነዚህን አርሶ አደሮች ስሜት በማጠናከርና ድክመቶቹን ለማረም የሚያግዙ ሌሎች እርምጃዎችን በመውሰድም ሚሊዮኖች የኤክስቴንሽን መርሃ ግብሩ አካላት እንዲሆኑ የሚያስችል መንገድ ተቀየሰ፡፡

ይህንን መርሃ ግብር ለአርሶ አደሩ በማስተዋወቅ ወደተግባር ከመግባት ጎን ለጎንም ለዚሁ መርሃ ግብር ስኬት ቁልፍ የሆኑ ሌሎች ስራዎችም ተከናውነዋል፡፡ ከእነዚህ መካከልም

አንዱ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ሰፋፊ የግብርና ምርምር ማእከላት ማስፋፋት፣ ምርታማነታቸው የተረጋገጡ መሰረታዊ የሆኑ ምርጥ ዘሮችን ለአርሶ አደሩ ማከፋፈልና ምርታማነትን ሊያጠናክሩ የሚችሉ ማዳበሪያንና መሰል ግብዓቶችንም አርሶ አደሩ በቅርብ የሚያገኝበትን መንገድ ማመቻቸት ይጠቀሳሉ፡፡ የምርምር ማእከላቱ ለአገሪቱ የተለያዩ መልክአ ምድራዊ ጸባያት የተመቹና ምርታማነትን በከፍተኛ መጠን ሊያሳድጉ የሚችሉ የእህል ዝርያዎችን በማውጣት፣ ዘመናዊ የአስተራረስ ስልትን ለአርሶ አደሩ በማስተዋወቅ ላይ አተኩረው ስራቸውን ተያያዙት፡፡

የኤክስቴንሽን መርሃ ግብሩን ትግበራ የተቀላጠፈና ውጤታማ ለማድረግ መንግስት በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የግብርና ማሰልጠኛ ተቋማትን ከፈተ፡፡ ከእነዚህ ተቋማት በልዩ ልዩ የግብርና ተያያዥ ሙያ ሰልጥነው የሚወጡትን ሙያተኞች በመላው አገሪቱ በማሰማራት ለአርሶ አደሩ የቅርብ ሙያዊ እገዛና ምክር እንዲሰጡ እየተደረገ ይገኛል፡፡ በዚህም አማካኝነት በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ የሚገኘው አርሶ አደር የእለት ግብርና ስራ በእውቀት ላይ የተመሰረተ ሆኗል፡፡

የተለያየ መጠንና አቅም ያላቸው ዘመናዊ የመስኖ ግንባታዎችን ጨምሮ በአገሪቱ የሚገኘውን ውሃ ለግብርና ልማት ማዋል የሚቻልበት ሰፊ ተግባርም ከኤክስቴንሽን ስራው ጎን ለጎን ተከናውኗል፤ በአሁኑ ወቅትም እየተከናወነ ይገኛል፡፡ የግብርና የመርሃ ግብሩን ትግበራ ተከትሎ ምርታማነት በእጅጉ እየተሻሻለ መጣ፡፡ በዚህም አማካኝነት ዝናብን አንጋጦ እየጠበቀ በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ከሚያርሰው የኢትዮጵያ አርሶ አደር መካከል አብዛኛው ሁለትና ከዚያም በላይ ጊዜ ማረስ እንደሚቻል አርሶ አደሩ አረጋገጠ፡፡

ይህም በመላው አርሶ አደሩ ዘንድ ከፍተኛ መነቃቃትና መለወጥ ይቻላል የሚል መንፈስ ተቀጣጠለ፡፡ ከእውቀት ማነስና ከቆየው ዝቅተኛ የስራ ባህል ጋር ተያይዞ ለኤክስቴንሽን መርሃ ግብሩ ብዙም ቁብ ያልነበራቸውና በመርሃ ግብሩ እንዲታቀፉ በየጊዜው ይወተወቱ የነበሩት ሳይቀሩ በተገላቢጦች የልማቱ ተሳታፊ ይሆኑ ዘንድ ራሳቸው መጠየቅ ጀመሩ፡፡

የልማት ስትራቴጂውና እርሱን ተከትሎ የተወሰደው እርምጃ የአገሪቱን የግብርና ዘርፍ ላይ መዋቅራዊ ለውጥ መጣ፡፡ የግብርና ልማቱ በመላው የአገሪቱ ገጠር ክፍል እየተቀጣጠለ በመምጣቱም የአርሶ አደሩ ኋላቀር የአስተራረስ ዜዴ ወደዘመናዊነት እየተለወጠ፤ ምርታማነቱም በየዓመቱ የሚያመረቃ እድገትን ማሳየት ያዘ፡፡ በ1980ዎቹ መጀመሪያ ላይ

ከ60 ሚሊዮን ኩንታል የማይበልጥ የነበረው አገራዊ የግብርና ምርት መጠን በአሁኑ ወቅት ከ280 ሚሊዮን ኩንታል ልቋል፡፡

ብዙውን ጊዜ ከእጅ ወደአፍ ሌላ ጊዜ ደግሞ ጦሙን ያድር በነበረው አርሶ አደር ዘንድም በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚያመረቃ ለውጥ ታየ፡፡ ቁጥሩ ከፍተኛ የሆነ አርሶ አደር ከእለት ጉርሱ አልፎ ለገበያ ሊያቀርበው የሚችለውን ምርት በትትራው ማጠራቀምን የተለመደ ተግባሩ አደረገው፡፡ ከዚህ ቀደም ሰርቶ የሚያሰራ ፖሊሲና ስትራቴጂ በማጣቱ የተነሳ የእለት ጉርሱን እንኳ በወጉ ማሸነፍ ተስኖት ለዘመናት የኖሩ አያሌ ኢትዮጵያዊያን አርሶ አደሮች የዘውትር ጭንቅ የነበረውን የእለት ጉርስ ድል ከመንሳት አልፈው ስለወደፊቱና ስለተሻለው ህይወታቸው ማለውን ተያያዙት፡፡

በትተራ ያከማቹትን ምርት ለገበያ በማቅረብ ጥሪት መሰብሰብ ችለዋልና የድህነት መገለጫ ከሆነው ኋላ ቀር የአኗኗር ዘዬ መላቀቅን በማሰብ ጠንክረው መስራትን ተያያዙት፡፡ ለዝንት ዓለም ያለአንዳች መሻሻል ይኖሩበት የነበረውን የሳር ቤት ከዳን ቤት በቆርቆሮ ቀየሩ፤ እያደርም ሰፊና ዘመናዊ ቤት መገንባት የቻሉም በርካቶች ሆነው ታዩ፡፡ በርካቶች በታሪካቸው ለመጀመሪያ ጊዜ ለልጆቻቸው የተሻለ ምግብ ማቅረብንና ጥሩ ልብስ አልብሶም ወደትምህርት ቤት መላክ የሚችሉበትን ደረጃ ተቀዳጁ፡፡

የግብርና ልማት ፖሊሲውና ስልቱ አገሪቷ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ ከእጅ ወደአፍ የግብርና ስራ ወጥተው ወደባለኃብትነት የተለወጡ አያሌዎችንም ማፍራት ጀምሯል፡፡ ይህንን ደረጃ የተቀዳጁትን አያሌዎች ከሚወክሉት አርሶ አደሮች መካከል የኦሮሚያ ክልሉ አቶ እሸቱ እርዳቸው ይጠቀሳሉ፡፡ ከአዲስ አበባ ከተማ መቶ ኪሎ ሜትር ርቀት በምትገኘው አድኣ ወረዳ ድሬ አራርቶ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት የ58 ዓመቶ እኚህ አርሶ አደር ከ1983 ዓም በፊት ሁለት ሄክታር ከማትበልጠው የእርሻ መሬታቸው ውጭ ለእርሻ ተግባራቸው የሚጠቀሙበት የራሳቸው የሆነ ጥማድ በሬ እንኳ አልነበራቸውም፡፡

የበሬ ግንባር ከምታክለው መሬታቸው በስተቀር ምንም ተስፋ ስላልነበራቸው በከፋ ድህነት ውስጥ ሲማቅቁ ከግማሽ የሚልቀውን እድሜያቸውን ያሳለፉት አቶ እሸቱ ዛሬ ለማመን በሚያዳግት ሁኔታ አድገዋል፤ ተመንድገዋል፡፡ መንግስት ለዘረጋው የግብርና ልማት መርሃ ግብር ምስጋና ይገባውና በመርሃ ግብሩ አማካኝነት ያገኙትን ድጋፍ በመጠቀም ሌት ተቀን በመስራታቸው ከ14 ሚሊዮን ብር የሚልቅ ኃብት ማካበት ችለዋል፡፡ ይህም

ከግብርናው ስራ ባሻገር በሌላ የኢኮኖሚ ዘርፍ ለመሰማራት የሚያበቃቸውን አቅም እንደፈጠረላቸው በአንድ ወቅት ተመክሯቸውን ባካፈሉበት አንድ መድረክ ላይ ሲገልፁ አድምጫቸዋለሁ፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት የግብርና ልማት ስልት ፍሬ የሆኑትን እኚህን አርሶ አደር ለአብነት አነሳሁ እንጂ እርሳቸውን የመሰሉ በርካቶችን አዲሱቷ ኢትዮጵያ ፈጥራለች፡፡ የእነዚህን አርዓያ የተከተሉ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ የአገሪቱ አርሶ አደሮችም የልማት መስመሩን እየተከተሉ በግስጋሴ ላይ መሆናቸውንም ብዙዎቻችን በየእለቱ እየታዘብን ነው፡፡

በኢትዮጵያ አዲስ የተዘረጋው የፖለቲካ ኢኮኖሚና እርሱንም ተከትሎ የተቀየሰው የግብርና ልማት ስልት በዜጎች ዘንድ በተለይም በከፋ ድህነት ውስጥ በኖረው የገጠሩ ህዝብ ውስጥ ከፍተኛ መነቃቃትንና የመለወጥ መንፈስን ፈጥሯል፡፡ ይህም በአዲሱ ስርዓት ቁርጠኛ አመራር የታለመውን ብሄራዊ የመታደስ ራእይ እውን ለማድረግ የሚያስችል አቅም እየገነባ መሆኑን ብዙዎች ያምናሉ፡፡

የግብርና ልማት መንገዱ የአርሶ አደሩን ህይወት ከመለወጥና በዜጎች ውስጥ መነቃቃትን ከመፍጠር ጎን ለጎን የአገራዊውን ምጣኔ ኃብትን አቅምም በመገንባትና ሌሎች የአገሪቱ ማህበራዊ ችግሮችን በማስወገድ ላይ ይገኛል፡፡ ከጥቂት ዓመታት ወዲህ እየተጠናከረ ለመጣው ብሄራዊ የውጭ ምንዛሪ እድገት ቁልፍ ሚና እየተጫወተ ያለው በአነስተኛ ማሳ ላይ የተሰማሩትን አብዛኛዎቹን የአገሪቱ አርሶ አደሮች ለስራ በማነሳሳት ለውጤት ያበቃው የግብርና ልማቱ ስልት ነው፡፡

የግብርና ልማት ስልቱ ስኬት ለዘመናት በባዶ ሜዳ እየተንገዳገደ ለአገሩቱም ሆነ ለዜጎቿ አንዳች ሳይፈይድ የኖረው ብሄራዊው ኢኮኖሚያዊ እንዲነቃቃ ኃይልና ጉልበት ሲሆነው መታየት ጀምሯል፡፡ በ1980ዎቹ መጀመሪያ ላይ በምንም ዓይነት መለኪያ ይህ ነው የሚል ደረጃ ለመስጠት ያስቸግር የነበረው ምጣኔ ኃብት በዋነኝነት በግብርናው የልማት ስልት አማካኝነት ወጉን የጠበቀና ሊነገርለት የሚችል ደረጃን እየያዘ ይገኛል፡፡ ከባዶ ተነስቶም በየዓመቱ እመርታን እያሳየ በዓለም አቀፍ ደረጃ በፍጥነቱና በጥንካሬው ሊጠቀስ የሚችል ቁመናን ተላብሷል፡፡

በተለይ ባለፉት አስር ዓመታት በአገሪቱ በተከታታይ የተመዘገበው ምጣኔ ኃብታዊ እድገት መሰረቱ ግብርናው መሆኑ ዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ጭምር ያስደመመ ስኬት ሆኖ

ተስተጋብቷል፡፡ ዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት በቅርቡ ባወጣው የዓለም አገራት ምጣኔ ኃብታዊ ሁኔታ ግምገማዊ ሪፖርት ላይ እንደተመለከተው ከጥቂት ዓመታት ወዲህ በርካታ የአፍሪካ አገራት ምጣኔ ኃብታዊ እድገት ማምጣት የቻሉት ነዳጅን ጨምሮ የተለያዩ የተፈጥሮ ማእድናትን በማግኘታቸው ነው፡፡

ኢትዮጵያ ግን በተከታታይ እያስመዘገበችው ካለው የምጣኔ ኃብት እድገት በስተጀርባ ነዳጅን የመሰለ የተፈጥሮ ኃብት የለም፤ ለእድገቱ ቁልፉን ሚና እየተጫወተ ያለው የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ነው በማለት ባንኩ ገልጿል፡፡

ይህም የሚያሳየው የአገሪቱ ምጣኔ ኃብታዊ እድገት ዘርፈ ብዙ አገራዊ ጥረት የታከለበትና በብዙ መልኩም ሁለንተናዊነትን የተላበሰ በመሆኑ በነዳጅ ከሚገኙት ምጣኔ ኃብታዊ አቅሞች የተሻለና ዘላቂነት ሊኖረው የሚችል መሆኑንም የዘርፉ ምሁራን እየመሰከሩ ናቸው፡፡ የዚህ ዓይነቱ የልማት ስልት በህዝብ ተሳትፎ የሚተገበር በመሆኑ ውጤታማነቱ ከሌሎቹ ነዳጅ ያገኙ አገራት የላቀ ነው፤ ለዚህም ትልቁ ማሳያ በኢትዮጵያ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ብቻ ፖሊሲው የፈጠረላቸውን ምቹ ሁኔታ የተከተሉ ሚሊዮኖች ከድህነት መውጣታቸው መሆኑንም ምሁራኑ ይገልፃሉ፡፡

የግብርናው ዘርፍ አጠቃላይ ብሄራዊ ምጣኔ ኃብቱ እንዲጠናከር በማድረጉ ከ20 ዓመታት በፊት ከአንድ መቶ የአሜሪካ ዶላር ያንስ የነበረው የዜጎች ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ በአሁኑ ወቅት ከ500 ዶላር በላይ እንዲያድግ ማስቻሉንም የአገሪቱን ምጣኔ ኃብታዊ ሁኔታ የገመገሙ ዓለም አቀፍ ሪፖርቶች ጭምር አረጋግጠዋል፡፡

ሌላው የግብርናው የልማት ስልት ያመጣው ፋይዳ አገራዊ ምጣኔ ኃብታዊ መነቃቃትን መፍጠሩ መሆኑም ይነገራል፡፡ የአርሶ አደሩ ገቢ ከመጨመሩ ጋር ተያይዞ በተለይ የአገሪቱ ክፍል የገጠር ክፍሎች ልማት እንዲፋጠን ምጣኔ ኃብታዊ እንቅስቃሴዎች እንዲፈጠሩ ምክንያት እየሆነ መጥቷል፡፡ የገቢው እየጨመረ መምጣት በገጠሩ ክፍል ያለው ህዝብ የሸቀጦች ፍላጎትን አሳድጓል፤ ይህም የሸቀጥና አገልግሎት አቅርቦትን ለማሳደግ የሚያስችሉ ኢንቨስትመንቶች በአገሪቱ እንዲስፋፉ ምክንያት በመሆን ላይ ይገኛል፡፡

የግብርና ልማት መንገዱ ምርትና ምርታማነትን በማሳደጉ ተፈጥሯዊም ሆነ ሰው ሰራሽ አደጋዎችን ተከትሎ ሊከሰት የሚችልን ድንገተኛ የምግብ እጥረት ችግርን መከላከል

የሚያስችል አገራዊ የእርዳታ አቅርቦት አቅምም ፈጥሯል፡፡ በአሁኑ ወቅት በርሃብ ምክንያት ህይወቱ የሚጠፋ ዜጋ በአገሪቱ አይኖርም፤ በምግብ እጥረት ችግርም ሳቢያም ከዛሬ ነገ ይመጣል የሚባልን የውጭ እርዳታ እየጠበቁ መቆየትም ቀርቷል፡፡

ምክንያቱም ለግብርናው የልማት መንገድና ለአርሶ አደሩ የእለት ተለት ትጋት ምስጋና ይግባውና አገሪቱ ለክፉ ጊዜ ብላ ካስቀመጠችው የምግብ እህል ቆንጥራ ለተጎጂዎች ማደል የሚያስችላትን ስርዓት ዘርግታለች፡፡ ስኬቱ ለዘመናት የኖረውን የውጭ እርዳታ ጠባቂነት አባዜ ሙሉ በሙሉ ሊወገድ የሚችልበትን አቅም በመፍጠር ላይ ናት፡፡

ኢትዮጵያ የግብርና ልማት አቅጣጫ መላውን አርሶ አደር በቀጥታና በንቃት ማሳተፍ የባለቤትነት ስሜትን መፍጠር መቻሉና የመርሃ ግብሩ የትግበራ ስልቶችና ዓላማውም የአገሪቱን ተጨባጭ እውነቶች መሰረት ያደረገ መሆኑ ለስኬቱ የሚጠቀሱ ቁልፍ ሁኔታዎች መሆናቸውም በብዙዎች ተነግሮለታል፡፡

ኢትዮጵያ አነስተኛ ማሳ ያላቸውን አብዛኞዎቹን አርሶ አደሮች በስፋት በመጠቀም ያሳየችው ይህ ለውጥ ለብዙ ዘመናት በተለይ በበለፀጉት አገራት ዘንድ የማይታሰብ ተደርጎ ሲወሰድ የቆየውን አንድ አመለካከት ውድቅ አድርጓል፡፡ በእነዚህ አካላት እምነት በማደግ ላይ የሚገኙ የዓለም አገራት የግብርናውን ዘርፍ ተጠቅመው የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥም ሆነ ምጣኔ ኃብታቸውን መገንባት የሚችሉት ሰፋፊና ዘመናዊ እርሻዎችን በማስፋፋት እንጂ አነስተኛ ማሳዎችን በመጠቀም አይደለም፡፡ አነስተኛ ማሳ ላይ የሚካሄዱ የግብርና ስራዎች ራስን ለመመገብ እንኳ የማያስችሉ ለአገር ምንም የማይፈይዱ ተደርገው ነበር በእነዚህ አካላት የሚታሰበው፡፡ አሁን ግን ይህ አስተሳሰብ ጥያቄ ውስጥ መውደቁን ብዙዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ እየገለጹ ይገኛል፡፡

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ስር የሚገኙ የተለያዩ አካላትን ጨምሮ በርካታ የልማት አጋር የሆኑ አገራትና ዓለም አቀፍ ተቋማትም ይህንን በማረጋገጥ የኢትዮጵያን የልማት አቅጣጫ አወድሰዋል፤ ለሌሎች በልማት ወደኋላ ለቀሩ አገራትም አርዓያ ሊሆን እንደሚችል መነትነት ጀምረዋል፡፡

ይህንን አቋም በማስተጋባት በቅርቡ ተግባራዊ እርምጃ እንዲወሰድ አዲስ መርሃ ግብር ከቀየሱት መካከል አንዷ አሜሪካ ናት፡፡ ከሁለት ዓመት በፊት የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊን ጨምሮ ሶስት የአፍሪካ አገራት መንግስታት የተሳተፉበትና

በምግብ ዋስትና ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው ላይ የመከረ ጉባኤ በአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጋባዥነት እዚያው አሜሪካ ውስጥ ተካሂዶ ነበር፡፡ በዚህ ወቅት አቶ መለስ የአገራቸውን የልማት መንገድ አስመልክተው ያቀረቡት ተሞክሮ ተቀባይነትን አግኝቷል፡፡ ባራክ ኦባማም የኢትዮጵያ መንግስት የግብርና ልማትን በማጠናከር የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ የሚያስችል ፖሊሲ ስራ ላይ ማዋሉን በመግለጽ የዚህ ዓይነቱ ፖሊሲ በሌሎች አገራት መተግበር እንዳለበት በአሜሪካ መንግስት በኩል አቋም መያዙን ይፋ አድርገዋል፡፡

ለዚሁ ፖሊሲ ማስፈጸሚያ የሚሆን በብዙ ቢሊዮን የሚቆጠር በጀት ተመድቧል፡፡ ኢትዮጵያም ይህንን ፖሊሲዋን አጠናክራ እንድትቀጥል ሌሎች የተመረጡ የአፍሪካ አገራትም የዚሁ መርሃ ግብር ተጠቃሚዎች ይሆናሉ ተብሏል፡፡

ከሳምንታት በፊት በአሜሪካ ዋሽንግተን ከተማ በተጠራው የአሜሪካና አፍሪካ አገራት የመሪዎች ጉባኤ ላይም ይህ የኢትዮጵያ ስኬት ተወድሷል፡፡ የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማሪያም ደሳለኝ የግብርና ልማት አቅጣጫቸውንና የምግብ ዋስትና መርሃ ግብራቸውን ስልቶችና እስካሁን ያሳዩትን ስኬቶች አስመልክቶ ልምዳቸውን ለዚህ ዓለም አቀፍ መድረክ አካፍለዋል፡፡ የጉባኤው ተሳታፊ የሆኑት የአህጉሪቱ መሪዎችም የኢትዮጵያን የግብርና ልማት ስልት በየአገሮቻቸው ለመተግበር ከፍተኛ መነሳሳትን አሳይተዋል፡፡

ሰሞኑን ደግሞ አዲስ አበባ ውስጥ የአፍሪካ ግሪን ሪቮሉሽን በሚል መሪ ቃል የአፍሪካ አገራት መሪዎችና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የተሳተፉበት ጉባኤ ተካሂዷል፡፡ ጉባኤው በምግብ ዋስትናና የተፈጥሮ ኃብት ጥበቃ ችግሮች ላይ ትኩረት ሰጥቶ የመከረ ሲሆን ይህንን ችግር በመቅረፍ ረገድ ከየትኛውም የአፍሪካ አገር የተሻለ ተብሎ የቀረበው መልካም ተመክሮ የኢትዮጵያ ነበር፡፡

የተፈጥሮ ኃብትን አጠናክሮ በመጠበቅና የምግብ ዋስትና ችግርን በመቅረፍ ሂደት አነስተኛ ማሳ ላይ የተሰማራው አብዛኛው የአፍሪካ አርሶ  አደር ቁልፍ ሚና ሊጫወት የሚችል ስለመሆኑ ኢትዮጵያ ተጨባጭ ማሳያ ናት ሲሉ በጉባኤው ላይ የተሳተፉ አንዳንድ ባለሙያዎችና የአፍሪካ መንግስታት ባለስልጣናት ሲገልፁ ተደምጠዋል፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት ግብርናው የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣ ድህነትን ለመዋጋትና ብሄራዊ ምጣኔ ኃብትን ለማጠናከር የሚያስችል ቁልፍ ዘርፍ መሆኑን በመገንዘብ ለዘርፉ መበልጸግ

እያሳየው ያለው ቁርጠኝነትም በተለያዩ ዓለም አቀፍ አካላት ተደንቋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ እነዚህ አካላት የሚያነሱት አንዱ የአገሪቱ መንግስት ቁርጠኝነት ማሳያ ከአጠቃላይ ዓመታዊ የአገሪቱ በጀት ከ17 በመቶ በላይ የሚሆነውን ለግብርና ልማት መመደቡ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ላለፉት ዓመታት ለዘርፉ እየመደበችው ያለው ዓመታዊ በጀት ከሌሎች የአፍሪካ አገራት ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛና ብቸኛ መሆኑም ይነገራል፡፡ ምንም እንኳ የአፍሪካ መሪዎች የግብርናውን ዘርፍ ለማጠናከር አገራት ከአጠቃላይ ዓመታዊ በጀታቸው አስር በመቶውን ለዘርፉ ማጠናከሪያ እንዲያውሉት ከዓመታት በፊት ውሳኔ በማሳለፍ ቃል የገቡ ቢሆንም ይህንን ማሳካት የቻሉት ጥቂቶች ብቻ ናቸው፡፡ ከዚህ አንጻር ኢትዮጵያ የገባችውን ቃል ከማክበር አልፋ ብዙ ርቀት መጓዟ በብዙ ዎች ዘንድ ተደንቋል፣ ለዘርፉ እድገትም ይህ ቁርጠኝነቷ ቁልፍ ሚና መጫወቱም ተመልክቷል፡፡

ምርታማነቱ ዘላቂነት እንዲኖረውና አርሶ አደሩም በምርቱ የሚገባውን ጥቅም በማግኘት ለበለጠ ስራ እንዲተጋ የሚያስችሉ በርካታ መዋቅራዊ ለውጦችም በዘርፉ ዙሪያ ተካሂደዋል፡፡ ከእነዚህ መካከል አንዱና ምናልባትም ቁልፍ የሚባለው በመንግስት አማካኝነት የተዘረጋው የግብርና ምርት የገበያ ስርዓት ነው፡፡ በዚህ የገበያ ስርዓት አማካኝነት አርሶ አደሩ ላመረተው ምርት ተገቢውን ዋጋ እንዲያገኝ፣ ምርቱንም በአቅራቢያውና በሚያመቸው መንገድ ለገበያ እንዲያቀርብ የሚያስችል ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

ይህ የገበያ ስርዓት ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቀና አርሶ አደሩም ከአገር ውስጥ ባሻገር ምርቱን ለውጭ ገበያ ጭምር ማቅረብ የሚችልበት ነው፡፡ ይህ ስርዓት በራሱ በአፍሪካ አዲስ ከመሆኑ ሌላ ውጤታማነቱም የሚያመረቃ ሆኖ ታይቷል፡፡ እናም ብዙዎች የአፍሪካ አገራት ይህንን መሰል ስርዓት ለመዘርጋት የኢትዮጵያን ተመክሮ በመውሰድ ላይ ይገኛሉ፡፡

የኢትዮጵያ የግብርና ልማት ስልት በአገሪቱ አርሶ አደሮች የሚመረቱ የተለያዩ የግብርና ምርቶች ከኢንዱስትሪው ጋር ቁርኝት ፈጥረው ዋነኛ የአገር ውስጥ ጥሬ እቃ አቅራቢዎች ሊሆኑ የሚችሉበትንም መንገድ ያመቻቸ ነው፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ወቅት በርካታ የአገር

ውስጥ የአግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች የሚጠቀሙት ከአርሶ አደሩ የሚቀርብላቸውን ጥሬ እቃ እየሆነ በመምጣት ላይ ይገኛል፡፡

እናም በዓለም በተለይም አፍሪካን የመሰሉ በልማታቸው ወደኋላ የቀሩ ክፍሎች ውስጥ ስር እየሰደደ የመጣውን የምግብ ዋስትና ችግር ለመቆጣጠር ህይወታቸውን በአነስተኛ ማሳ ላይ የመሰረቱ አርሶ አደሮችን በስፋት መጠቀም ዓይነተኛው መሳሪያ መሆኑን ብዙዎች ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ እየተካሄዱ ያሉ ዓለም አቀፍ ጥናቶችም በማረጋገጥ ላይ ናቸው፡፡ ጥናቶቹ እንደሚሉት አፍሪካ ውስጥ አብዛኛው የግብርና ስራ የሚከናወነው አነስተኛ ማሳ ላይ ነው፤ እነዚህ አርሶ አደሮች ተገቢ የሆነው እገዛ ከተደረገላቸው የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን ሌላ ተጨማሪ ተአምርም መፍጠር ይችላሉ፡፡ እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች የገጠር ልማትን ማፋጠን የሚያስችሉ ሌሎች በርካታ ማህበራዊና ምጣኔ ኃብታዊ አቅም ያላቸው መሆኑንም ጥናቶቹ አረጋግጠዋል፡፡

ይህ የሚያረጋግጠው በመጀመሪያው የትግበራ ዘመን አንዳንዶች ሊያጣጥሉት የሞከሩት የኢትዮጵያ መንግስት የግብርና ልማት ፖሊሲና የትግበራ ስልት ትክክለኛ መሆኑን ነው፡፡ ጤናማ አመለካከትና ሚዛናዊ አተያይ ያለው ማንም አካል ይህንን እውነት ለመቀበል ብዙ የሚጠበቅበት አይመስለኝም፡፡

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ የግብርና ልማት አቅጣጫ ከአገር አልፎ ለአፍሪካ አገራት ጭምር አለኝታ ለመሆን መብቃቱ ሁላችንንም ሊያስደስተን ይገባል፡፡ አገሪቱ በዓለም አቀፍ መድረኮች እላይ በተጠቀሰው መልኩ እየተወደሰች መነሳቷ የአገራችንን የቆየ መጥፎ ገጽታ በመቀየር በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂነትን ያተረፈልን በመሆኑ መሪዎቻችን ሊመሰገኑ ይገባቸዋል እላለሁ፡፡ የአገራችንን ሁኔታ በሚገባው ደረጃ ለመለወጥ አሁንም ብዙ መስራት ይጠበቅብናልና በስኬታችን በመነሳሳት ጠንክረን ልንተጋ ይገባል፡፡